# ዘመቻ “”አባ መላኩ”

# በዲሲ ር/አ/ደ/ሰ/ቅ/ ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ

# አባ መላኩ ሠራዊታቸውን አሰለፉ

ጳጉሜ ፭ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. (September 10, 2015)

በአቡነ ፋኑኤል (አባ መላኩ) ፊታውራሪነት የሚመራው “”ዘመቻ አባ መላኩ” የተሰኘው ሁሉ አቀፍ ዘመቻ ሰሞኑን በአትላንታና በዋሺንግተን ዲሲ ከተማዎች ውስጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። የዘመቻው ትልቁ ግብ ስለሰባዊነትና ስለ ኢትዮጵያዊነት የሚቆረቆሩትን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ማዳከም እንደሆነ ታውቋል። ይህ በተለይም በዲያስፖራ ያለውን ተቃውሞ እንዳይጠነክር ለማፈን የታለመ ዘመቻ ነው። ለዘመቻው አፈጻጸም የተነደፈው ስትራቴጂው ሦስት አማራጮችን ጎን ለጎን አድርጎ መንቀሳቀስን ያካተተ ነው። እነዚህም፤

- ከተቻለ እያንዳዱን ቤተክርስቲያን በአባ መላኩ ቁጥጥር ስር ማዋል፣
- ካልተቻለ ደግሞ ሥርዓተ አልበኝነትን በማስፈን መበጥበጥ። በተለይ የጸረ - ወያኔን ጎራ በትርምስ ማወክና ስለወገኑና ስለ እምነቱ የሚቆረቆረው ሁሉ በተረጋጋ መንፈስ መኖር እንዳይችል ማድረግ ነው። ይሄ በአገር ቤት የሚደረገው አይነተኛ መገለጫው ነው።
- በአንድ ከተማ ውስጥ ሌላ ቤተክርስቲያን በተመሳሳይ ስም በየማእዘኑ መክፈትና፣

አባ መላኩ፣ ከአባ ማትያስ (በንቡረዕድ ኤልያስ በኩል) የሚሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥድፊያ ላይ ናቸው። በተለይም በዉጭ የሚገኘው ምዕመን ወቅታዊ ሁኔታዎችን ለመከታተልና ለማገናዘብ ጊዜ ስሌለው ለዘመናችን ሆድ-አደሮች አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል። አባ መላኩ እነዚህን አጋጣሚዎች ተጠቅመው በተለይም የዲሲን ሕዝብ መቆጣጠር ይፈልጋሉ። ለዲሲ ሕዝብ ያላቸውን ንቀት ሲያሳዩ “የዲሲ ሕዝብ ሰልፍ የሚወጣው ስትረስ (stress) ሲይዘው ብቻ ነው። ስቴት ዲፓርትመንት እየሄድ የሚጮኸውም በዚህ ምክንያት ነው። ዝም በሉት፣ ጮሆ ጮሆ ስትረስ ሲለቀው ያቆማል ብለው በድፍረት የሚናገሩት። የተቃዋሚውን ጎራ ማሸነፍ ባለመቻላቸው አሁን መረጋጋት ያለበትን ቤተክርስቲያን ሁሉ ማወክ ትልቁ ግባቸው አድርገው ነው የሚንቀሳቀሱት።

## አባ መላኩ ማን ናቸው የሚለውን በመጨረሻ ስለሚቀርብ በቁጥር 5 ላይ ያለውን ይመልከቱ

በዲሲ አካባቢ ሁለት አንጋፋ ቤተክርስቲያናትን “መቆጣጠር አለባችሁ፣ ወይም ብጥብጥ በመፍጠር ማዳከም አለባችሁ” ተብለው በመጀምሪያ ዙር “”ዘመቻ አባ መላኩ” ፈተና ላይ የገቡት፤ ር/አ/ደ/ሰ/ ቅ/ማርያምና ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ናቸው። ይህን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ ለጥቃቅን ጥቅማ ጥቅሞች በሚያገበድዱ የዉስጥ አርበኞች ምክንያት ነው። አንዳንዴ እንዴት ሆነው እንደሚያስቡም ለመረዳት በጣም ያስቸግራል። ከእነዚህ ግለሰቦች ወያኔን ተቃዋሚ ናቸው የሚባሉም ይገኙበታል። ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ከስጋው ጦመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ የሚሉ ይመስላል። በአንድ በኩል የሰይጣን ሥራ የሚሰራውን የሰውን ልጆች እንደበግ የሚያርደውን የወያኔን መንግስት ዓላማ እያስፈጸሙ፣ በሌላ በኩል ወያኔን የሚቃወሙ መስለው ለመታየት የሚሞክሩ በርክተዋል።

ለምሳሌ “”ዘመቻ አባ መላኩ” በቅርብ ጊዜ በአትላንታ ከተማ የተደረገውን ለማወቅ ከፈለጉ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመንካት የዘመቻውን ተመሳሳይነት እንዳለው መረዳት ይቻላል። (ሰንሰለቱን በመጫን ያንብቡ። ዘመቻ አባ መላኩ በአትላንታ ሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን)

## “የዘመቻ አባ መላኩ” መነሻ ትልቁ ምክንያት

አባ መላኩ ተሾመው ዋሺንግተን ዲሲ ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በስራቸው ለማድረግ ሞክረዋል፣ አድርገዋልም። በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ ያልቻሉትን በተመሳሳይ ስም ሌላ ቤተክርስቲያናት ይከፍታሉ። (አባ መላኩ በየቦታው የከፈቷቸውን አብያተ ክርስቲያናት አስታኮ የሚከፈላቸውን የገንዘብ ብዛትና ያካበቱትን ሀብት ምን ያህል እንደሆነ ወደፊት በዝርዝር ይቀርባል።) ለአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት “በንብረታችሁ አልገባባችሁም።” የሚል የሐሰት ደብዳቤ በመጻፍ እያሞኙ ለመቆጣጠር ችለዋል። የዲሲ ዘመቻን ለየት የሚያደርገው አባ መላኩ ማንነታቸው በአካባቢው ሕዝብ ስለሚታወቅ በቀላሉ በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ አልቻሉም። በአሁኑ ወቅት ዲሲ ላይ በስውር የተቀነባበረው **‘ዘመቻ አባ መላኩ’** በቅርቡ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ በተደረገው ክስተት ፍንተው ብሎ ታይቷል።

ይህም ልዩ ክስተት የሆነው ሊቢያ ላይ ሰማዕትነትን የተቀበሉት ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ምክንያት ነው። ለነዚህ ሰማዕታት መታሰቢያ በተደረገው እንቅስቃሴ ማ ምን እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል። ይህን አስመልክቶ ዲሲና ቨርጂንያ ግዛቶች ዉስጥ ሁለት ዝግጅቶች ተደርገው ነበር። የመጀመሪያው ዝግጅት May 10, 2015, በዋሽንግተን ሞኑመንት አጠገብ በዲሲ አካባቢ ያሉ የሶስቱም እምነት ተከታዮችና ለሰባዊነትና ዲሞክራሲ የሚታገሉ ኃይሎች አዘጋጅነት የተደረገው ነው። በዚህ ዝግጅት ላይ ር/አ/ደ/ሰ/ ቅ/ ማርያም ቤተክርስቲያን

ግንባር ቀደምነት ያለው ተሳትፎ ያደረገችበት ነበር። በሌላ በኩል በJune 14, 2015፣ ፌርፋክስ ውስጥ በኬና ቴምፕል በመምህር ዶ/ር መምህር ዘበነ ለማ መሪነትና በአባ መላኩ ትዕዛዝ የተደረገው ዝግጅት ነው። በሞኑመንቱ ዝግጅት ላይ ትላልቅ አባቶች ሲገኙ የደብረ ሰላም ስብከተ ወንጌል ኃላፊ የነበሩት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ የሰንበት ት/ቤቱን ይዘው አልተገኙም ነበር። በቦታው ላለመገኘት የተለያየ ምክንያት ቢኖራቸውም “”**ትልቁ ችግራቸው በሊቢያ በታረዱት ሰበብ የወያኔ መንግስት ለምን ይወቀሳል? መንግስትን አንነካም፤ አንዳንዶቻችን አገር ቤት ፕሮጀክት ጀምረናል፣ ፕሮጀክታችን ይበላሽብናል ወ. ዘ. ተ. “** የሚል አንድምታ ያለው ነበር። ከላይ እንደተጠቀሰው በዋሺንግተን ሞኑመንት ላይ በተደረገው ሕዝባዊ የጩኸት ድምፅ ላይ አልተገኙም። በዋሺንግተን ሞኑመንት አጠገም የተደረግውን ዝግጅትን ለማደናቀፍ ብዙ ሙከራዎች ተደርገው ነበር። የአደናቃፊዎቹ ቡድንም ይሄው **“የወያኔ መንግስት በምንም መልኩ በአደባባይ ወቀሳ እንዳይቀርብበት** ማድረግ ነበር። በዋሽንግተን ሞኑመንት ላይ በተደረገው ሕዝባዊ የጩኸት ድምፅ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ከዚህ ቀደም ተዘግቧል። ለማስታወስ ያህል የሚቀጥሉትን ሰንሰለቶች በመጫን ቪድዮዎችን ይመልከቱ።

- Part 1 በዋሺንግተን ሞኑመብት ላይ የተደረገው ሕዝባዊ የጩኸት ድምፅ ክፍል 1
- Part 2 በዋሺንግተን ሞኑመብት ላይ የተደረገው ሕዝባዊ የጩኸት ድምፅ ክፍል 2

አባ መላኩ በቀጣም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚጠቀሙባቸው ሰራዊቶች አሏቸው። ከነዝህም ዉስጥ ጥቂቶቹ ቀጥለው ተዘርዝረዋል።

## 1. *መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ*

*መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ* የሊቢያው ሰማዕታት ዜና እንደተሰማ ጠዋት April 19, 2015 ለደብረሰላም ቅ. ማርያም ምዕመናን ልብን የሚነካ አገልግሎት በወቅቱ ሰጥተው ነበር። በተለይም አርብ April 24, 2015 በደብሩ በተደረገው የጸሎት አገልግሎት ዋና አቀነባባሪ ሆነው አገልግለዋል። በዚሁ ዕለት (Friday April 24, 2015) ቀሲስ ተስፋዬ “የዛሬው ጩኸት ወደ እግዚአብሔር ሲሆን፣ ሰሞኑን ግን በአደባባይ ለዓለም ሕዝብና መንግሥታት ጩኸታችንን እናቀርባለን።” በማለት ቦታውም **ዋሺንግተን ሞኑመንት አጠገብ** እንደሚሆን አወጁ። የመጀመሪያውን ጥሪ ያስተላለፉት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ በቦታው ሊገኙ ባለመቻላቸው ብዙ ሰዎች ገርሚቸው ይጠይቁ ነበር። መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ በሌላ በኩል፣ በዶ/ር መምህር ዘበነ ለማ አዘጋጅነትና በአባ መላኩ ባራኪነት የተደረገው ዝግጅት ላይ ተገኝተዋል። የዶ/ር መምህር ዘበነ ለማ ዝግጅት በተቻለ መጠን ወያኔ እንዳይኮንን ሆኖ የተዘጋጀ እንደነበር አብረው ከነበሩና ከዝግጅቱ ቪድዮ መረዳት ይቻላል።በመምህር ዶ/ር መምህር ዘበነ የተቀነባበረውን በJune 14, 2015 በKena Temple የቪድዮ ማስረጃዎች ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት በመጫን ይመልከቱ:-ሰይጣንን እምቢ በሉ በሚል ቀርቦ ነበር ብሎ የቀረበውን እዚህ ላይ በመጫን ይመለከቱ ።

*መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ* በኬና ቴምፕል ሲገኙ፣ ነገር ግን በዋሺንግተን ሞኑመንት ዝግጅት ስላልተገኙ እሳቸውንና የሚቀርቧቸው ወዳጆቻቸው ሲጠየቁ የሚሰጡት ምክንያት እርስ በርሱ የሚጣረሱ ናቸው። ለምሳሌ አንዱ የመጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ ደጋፊዎች የሚያቀርቡት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ሲወጡ የተጣሉ ባልና ሚስት ፓርኪንግ ሎት ቆመው ጠበቋቸው። ስለዚህ ዋሺንግተን ሞኑመንት ላይ በመገኘት ፋንታ ባልና ሚስትን ሊያስታርቁ ሄዱ። የሚል ነበር።

ለመሆኑ መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ ከአባ መላኩ ጋር ምን ያገናኛቸዋል? ጉዳዩ መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ ሹመት የተቀበሉት ከአባ መላኩ መሆኑን የሚቀጥሉት ለአቡነ ጳውሎስ የተጻፉትን ሁለት ደብዳቤዎች ማየቱ ይበቃል ። ምናልባት መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ የሚያገለግሉበትን ቤተክርስቲያን (ማርያምን) ትተው በሌላ ዝግጅት ለምን ተገኙ? በተለይም ህዝበ ክርስቲያኑን በአንደበታቸው ጠርተው ራሳቸው ለምን አልተገኙም ቢባል ሹመት የሰጧቸው አባ መላኩ ስለሆኑና ምናልባትም በድብቅ ያደረጉት ስምምነት ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። “መጋቢ ሃይማኖት” የሚለውን ማዕረግ የሰጧቸው አባ መላኩ ሲሆን የስልጣን ኃላፊነታቸውን ማየት ይቻላል። በ2004 ዓ .ም. አባ መላኩ ለቀሲስ ተስፋዬ መቆያ በ*2 ወራት ውስጥ* ሁለት ጊዜ ሹመት የሰጡበትን ***የሚከተሉትን ሁለቱን የሹመት ደብዳቤዎች መመልከት ይበቃል። እጅግ የሚያስገርመው ነገር 2 ወራት ባልሞላ ጊዜ ከፍተኛ እድገት ማግኘታቸውን የተገኘው ደብዳቤ ያሳያል።***

- *መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ* ጥር 24 ቀን 2004 ዓ.ም. ለአቡነ ጳውሎስ በተፃፈ ደብዳቤ የተሰጠው ሹመት የዋሽንግተን ዲሲ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና የሰንበት ት/ቤት ኃላፊ። [የሹመቱን ደብዳቤ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ፣ ቀሲስ ተስፋዬ የተሾመበት የሹመት ደብዳቤ በ 11 ተራ ቁጥር ላይ ተመልከት። ]
- *መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ* መጋቢት 15 ቀን 2004 ዓ.ም.ለአቡነ ጳውሎስ በተፃፈ ደብዳቤ ሁለት ወር ሳይሞላው የተሰጠው ሹመት እድገትን ይመልከቱ። የ ***ስብከተ ወንጌል ማደራጃና መምሪያ ኃላፊ***። ይህ ማለት ለመላው አሜሪካ ማለት ነው። (የሹመቱን ደብዳቤ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ፣ መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ የሹመት እድገት ብኤ ወር ዉስጥ የተሾመበት የሹመት ደብዳቤ በ 8 ተራ ቁጥር ላይ ይመልከቱ።) አስተውላችሁ ከሆነ በዚህ ደብዳቤ በቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ሚስቱን የፈታው መላከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይ የቁጥጥር መምሪያ ኃላፊ ተብሎ የተሾመበት ይታያል።

## 2. *ሊቀሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ*

ሊቀሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ በደ/ሰ/ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያን በዋሺንግተን ሞኑመንት የሰማዕታትን ጩኸት ለማሰማት በተደረገው ዝግጅት ላይ ተገኝተው ነበር ። በኋላ ግን በዶ/ር መምህር ዘበነ ለማ በተቀነባበረውና በአባ መላኩ "በተባረከው" ዝግጅት ላይም ተገኝተው ነበር። ሰሞኑን በተፈጠረው ሁካታ ላይ ሊቀሊቃውንት የዋሽንግተን ማርያም ባለአደራ ቦርድና ሊቀማዕምራን ዶ/ር አማረ ካሣዬን እንዲወርዱ ከጠየቁት መወገናቸው ታውቋል። በሊቀ ሊቃውንት አካባቢ ያሉ እንደሚናገሩት እሳቸውን ዋና አስተዳዳሪ ለማድረግና ረዳት **ሞግዚት ካህን** (ልክ እንደ አገር ቤቱ መንግስት የሚያዝ ሞግዚት ማለት ይመስላል) ሊመደብላቸው ነው ይባላል። ለሞግዚት አስተዳዳሪ ካህንነት ከታጬት አንዱ መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ ተስፋዬ መቆያ ወይም ርዕሰ ደብረ አብርሐም ናቸው ይባላል።

## 3. <u>አቶ አዲሱ አበበ</u>

አቶ አዲሱ አበበ ለረዥም ጊዜ ማርያም ዉስጥ ነባር አባልና ብዙ ተሰሚነት እንደነበራቸው ይታወቃል። ነገር ግን ከአባ መላኩና ከአባ ማትያስ ጋር በነበራቸው ቅርብ ግንኙነትም ይሁን ወይም የጡረታ ማስከበሪያ ፍለጋ አይታወቅም ማርያምን ለአባ መላኩ አሳልፎ ለመስጠት ብዙ ጥረዋል። የአቶ አዲሱ አበበ ቡድን በማርያም ባለአደራ ቦርድና በሊቀማእምራን ዶ/ር አማረ ካሣዬ ላይ የከረረ ተቃውሞ ማድረግ የጀመሩት አቶ ታደሰ ሲሳይ ከተወገዘ በኋላ እንደሆን ጉዳዩን እግር በእግር የሚከታተሉ ግለሰቦች ይናገራሉ። የአቶ አዲሱ ቡድን ብዙ ስምና አድራሻ የሌላቸው በራሪ ወረቀቶችን በማርያም ቤተክርስቲያን በየእሁድ ጠዋት ይበትኑ ነበር። የአቶ አዲሱ ቡድን መሆኑን የሚያመለክተው የሚወረወሩት ክሶች ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ነው። በMay 18, 2014 የተበተነው በራሪ ወረቀት <u>**አባ መላኩ ሊቀማእምራን ዶ/ር አማረ ካሣዬን እንዲያወግዙ የሚማጸን**</u> ነበር። ቀሲስ አማረ እንዲወገዙ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ሚስቱን ፈቶ የሚቀድሰውን ታደሰ ሲሳይ ለምን ተነካብን የሚል ነው - በገጽ 2 በ6ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለውን ይመልከቱ። (የበራሪ ወረቀቱን ግልባጭ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት በመጫን ማየት ይቻላል። <u>ለብዙ ወራት በስውር ሲበተን የነበረው አዲሱ አበበ የሚመራው ቡድን ከበተናቸው ወረቀቶች አንዱ</u> ።

አቶ አዲሱ አበበ ከአሁን በፊት አንዳንድ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ ከአባ መላኩ ጋር ስላነበራቸውም ሆነ በአሜሪካን ሬድዮ ድምፅ ላይ በሚዘግቡት ቤተክርስቲያንን የሚጎዳና የተዛባ የጋዜጠኛነት ሥራ በመስራቱ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ሰፋ ያለ ጦማር ጽፈውበት ነበር። ምናልባት አቶ አዲሱ የጋዜጠኝነቱን ችሎታና ለእውነት መቆሙን ለማሳየት መልስ ይሰጣል ተብሎ ተጠብቆ ነበር። (በአቶ አዲሱ ላይ የተፃፈውን ሙሉውን ንባብ ለማስታወስ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይመልከቱ። <u>አቶ አዲሱ አበበ- ሰይፈ ነበልባል ክርስትናና ጋዜጠኝነት ሲወሀዱ ወደ ሰይፈ ነበልባልነት ይለወጣሉ።</u>ምናልባት ከዲሲ ማርያም ከአባልነት ስለተገለሉም ይሁን ወይም ከአባ መላኩ ጋር ባላቸው ጥብቅ ግንኙነት አይታወቅም በቨርጅንያ ገብርኤል ምረቃ ላይ <u>ከአባ መላኩና ከአትላንታው ከመጋቤ ብሉይ አባ ኃይለ ሚካኤል</u> ጋር አብረው ተሳትፈዋል። ቪድዮዉን ለማየት የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ይመልከቱ። <u>አዲሱ አበበ በአባ መላኩ የታሰበው ክህነት እንዲሰጠው ደጅ ሲጠና።</u> ወይም ፎቶውን ቀጥሎ ተመልከቱ።



*አቶ አዲሱ አበበ ከአባ መላኩ ጋር የቨርጅንያን ገብርኤል ሲከፍቱ*

## 4. <u>ዶ/ር አክሊሉ ሐብቴ</u>

ከ18 ዓመታት በላይ በዲሲ ር/አ/ደ/ሰ/ ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ ቤ/ክ የቦርድ አባልና የቤተክርስቲያኑ አድራጊና ፈጣሪ ሆነው የቆዩ አዛውንት ናቸው። ሆኖም ግን ከባለአደራ ቦርድ ኃላፊነት ከወረዱ ጊዜ አንስቶ ደስተኛነት አይታይባቸውም። ዞሮ ወደ ባለአደራ ቦርድ

ለመምጣት ሙከራ በመድረግ ላይ ያሉ ይመስላሉ። ባለፈው እሁድ አውደምህረት ላይ ወጥተው እንደተናገሩት “አሁን ያለው የማርያም ባለአደራ ቦርድ በአስቸኳይ እንዲወርድ የሚል ነበር። ይህ አካሄድ መፈንቅለ ቦርድ ይመስላል። እንዳነጋገራቸው ከሆነ “በሚቀጥለው እሁድ ቅዳሴም ቆሞም ቢሆን አስቸኳይ ስብሰባ እንዲደረግና የባለአደራ ቦርዱ ወርዶ ምርጫ እንዲደረግ የሚል ነበር። በቤተክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብም ሆነ በማንኛውም ዲሞክራሲያዊ አሠራር መሰረት የአባላትን አንድ ሶስተኛው ፔቲሽን (petition) ካስፈረሙ በኋላ ቦርዱ ስብሰባ እንዲጠራ ይገደዳል። የነዶክተር አክሊሉ አካሄድ ደጋፊ አባላት ቁጥር ⅓ ኛ አይሞላም። ስለሆነም እያደረጉ ያለው የስርዓት አልበኝነት ወይም የማን አለብኝነት ይመስላል። በጣም የሚገርመው ግን በአባ መላኩ ትዛዝ የተላኩ የውጭ ተወርዋሪ ኃይሎች በጩኸት ለመበጥበጥና በግርግር ስልጣን ለማስመለስ ደፋ ቀና ማለታቸውን ቀጥለውበታል። ነገሩማ ኢትዮጵያ ዉስጥ እንዳየነው ወያኔዎች አንድና ሁለት ሰዎችን በመላክ የፖለቲካ ፓርቲ ሲያፈርሱ ታይቷል።

## 5. አባ መላኩ ማን ናቸው?

አባ መላኩ በአቡነ ጳውሎስ ዘመን **አቡነ ፋኑኤል** የተባሉት በአሁኑ ሰዓት የአቡነ ማትያስ ተወካይ ናቸው። አባ መላኩ በቤተክርስቲያን ላይ ያደረሱት ጥፋት ቀላል አይደለም። ምናልባት እንደምኞታቸው ከሆነ ፓትርያርክ ለመሆንም ያስባሉ። አቡነ ፋኑኤል ፓትርያርክ ለመሆን እንደሚያስቡ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። አንዳዶች እንደሚናገሩትና እንደውም ፓትርያርክ ሆነዋል ምክንያቱም አኗኗራቸውም ሆነ የሚያሳዩት ባህርይ ልክ ፓትርያርክ እንደሆኑ ነው። በጵጵስናቸው ዘመን፡-


*“የቀድሞው መላከ ኪዳን ቄስ ታደሰ የአሁኑ አቶ ታደሰ ትዳሩን አፍርሶ [የፍቺውን ወረቀት ለማየት ከፈለጉ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ። የታደሰ ሲሳይ ሕጋዊ የፍቺ ወረቀት ግልባጭ Tadesse Sisay & Enat Tadese official Divorce Paper State of North Carolina። በድፍረት መቀደስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፤ አልባሌ ሰው ሊያደርገው በማይችል አስነዋሪ ተግባር ላይ ሲልከሰከስ በመገኘቱ የቅስና ምሳሌነቱ ለመምህርነት በቂ ሊሆን አልቻለም። “ የአካባቢው ሊቀ ጳጳስ ነኝ ስለሚሉ እባክዎትን እንዲፈርዱ ቢጠየቁ አቡነ ፋኑኤልም ከመገሰጽ ይልቅ መለኩሴ ቆሞስ አባ ገብረ መድህን ብለው ሰየሙት። [ለማስታወስ ያህል ቆሞስ አባ ገብረ መድህን የሚቹን አቡነ ጳውሎስ ስም ነው።]* የሹመቱን ዝርዝር በይፋ የትወጀበት ዜና መመልከት ይቻላል።http://diretribune.com/amharic/?p=2169&

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ እንደ አቡነ ፋኑኤል ዓይነቱን ሲገልፁ ቤተ ክርስቲያናችን አዲስ ተክል ትላቸዋለች ብለው የጻፉትንየሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ይያንብቡ። አባ ፋኑኤል አዲስ ተክል ናቸው። የአቡነ አቡነ ፋኑኤል የጥፋት ብዛት ከልክ ሲያልፍም የሚቀጥለውን መግለጫ “አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ! ” በሚል የተላለፈውን መግለጫ ሙሉ ቃል የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ይመልከቱ: በአባ ፋኑኤል ላይ የተሰጠ መግለጫ በዓለም የሚሰራጭ። አንባቢ ሆይ በጣም የሚያስደነግጠው ግን አባ ፋኑኤል 'ፓትሪያርክ' የመሆን ፍላጎታቸው የማያውቅ ካለ የሚቀጥለውን አጭር መረጃ ይመልከቱ።

# አባ መላኩ ፓትርያርክ ለመሆን ልምምድ እያደረጉ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ እሆናለሁ ብለው የተስፋ ሕልም ያላቸው መሆኑን አባ መላኩ ከአሁኑ ጀምሮ የሚለብሱትንና የሚያደርጉትን ቆብ፣ እንዲሁም አርዌ ብርት በመመልከቱ ይፍረዱ።





አቡነ ጳውሎስ  አርዌ ብርት ይዘው

አቡነ ማትያስ አርዌ ብርት ይዘው



የኮፕቲክ አቡነ ሽኖዳ



የኮፕቲክ  ዳግማዊ አቡነ ቴዎድሮስ



*መጪው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ አርዌ ብርት ይዘው*

አባ መላኩ የ*ፓትሪያርክ ልብስ ለብሰው* የ፳፻፯ ዓ. ም. ጥምቀተ በዓልን በዋሺንግተን ዲሲ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሲያከብሩ የሚያሳይ ቪድዮ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት በመጫን ይመልከቱ።
[Timket Jan. 2015 Washington, DC - St. Michael Church]

# ማጠቃለያ

*ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው አቡነ ፋኑኤል በ* **"ዘመቻ አባ መላኩ"** *'ፓትሪያርክ' የመሆን ምኞታቸውን ለማሳካት ማንኛውንም ኃይላቸውን ከመጠቀም ወደ ኋላ እንዳምይሉ ነው።* ከፎቶግራፉና ከቪድዮው እንደምናየውና አንዳንዶችም እንደሚሉት አባ ፋኑኤል እንደ 'ፓትሪያርክ' እየኖሩ አይደለም ወይ? እጅግ የሚገርመው ግን አቡነ ማትያስ ለምን ይህንን ያህል ስልጣናቸውን ስጋፏቸውና ዓይን ያወጣ ስርዓተ ቤተክርስቲያን ሲያበላሹ ዝም ይሏቸዋል የሚል ነው። የዚህ ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበትን የአሜሪካ ስቴቶች እንደ አባ መላኩ ሊቆጣጠር፣ ሊበትንና ሊያዳክም የሚችል ስለማያገኙ ነው። ስለዚህም ብዙ ሹመት ፈላጊዎችና የአባ መላኩ አብሮ ጥቅም ተካፋዮች:- *አብረዋቸው የተሰለፉና ከሳቸው ሹመት የሚቀበሉ፣ እሳቸውን አውግዙልን ብለው የሚማጠኑ፣ የሳቸውን ቡራኬ ለመቀበል የሚሽቀዳደሙ የሚታዘዙትንሁሉ ከማድረግ የማይገቱ በመሆናቸው ህዝበ ክርስቲያኑ አባ መላኩን በየደረሱበት ሊጠይቃቸው ይገባል።* **"ዘመቻ አባ መላኩ"**ን ለማስቆምና የቤተክርስቲያን ሰላም እስከሚመጣ ድረሥ አጠፋ ዘመቻ የሚቀጥል ይሆናል።

*ዘመድኩን ከ ዲሲ*

dskmeotc12@gmail.com